# የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)
# UNITED ETHIOPIAN DEMOCRATIC FORCES (UEDF)

## አያገቡት ገብቶ÷ ችግርን ጎትቶ !!
## የአገር አንድነትና የሕዝብ ደኅንነት ጉዳይ የሁሉም ኃላፊነት ነው!

ውድ አገራችን ኢትዮጵያ ወርሃዊ ደመወዝ የሚከፈለውና የደንብ ልብስ የለበሰ ሠራዊት ሳይኖራት ሕዝቧ ለዘመናት ባሕር ተሻግረው ከመጡ የቅኝ ግዛት ተቀራማቾች÷ ልዩ ልዩ ሰበቦችን ተገን አድርገው ከቅርብም ከሩቅም ከዘመቱ ወራሪዎችና ከተስፋፊ ኃይሎች ጋር እየተፋለመ ደሙን እያፈሰሰና አጥንቱን እየከሰከሰ የኑሮ ደረጃ÷ ጎሣ÷ እምነትና ፃታ ሳይለይ በሚያኮራ አንድነቱ የአገሩን ዳር ድንበር÷ ነፃነትና ሉዓላዊነት አስከብሮ ኖሯል፡፡ ሕዝባችን በራሱ ስንቅና በባዶ እግሩ እየዘመተና አይከፍሉ መስዋዕትነት እየከፈለ ጠላቶቹን ድባቅ እየመታ አሳፍሮ በመመለስ የአገሩን አንድነት ጠብቆ ያቆየው በንፁህ አገራዊ ፍቅር እንጅ ከመንግሥት ውለታ ጠብቆም ይሁን አግኝቶ አልነበረም፡፡

ለአገሩ ቀናኢ የሆነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በክቡር መስዋዕትነቱ ጠብቆ ያቆየልንን አንድነት አርቆ ማየት የተሳነው የአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ቡድን ሥልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በተከተላቸው ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-ብሔራዊ ጥቅም ፖሊሲዎችና በወሰዳቸው አፍራሽ እርምጃዎች እነሆ አገራዊ አንድነት ተናግቶ÷ ለዘመናት የተገነባ የሕዝብ ትስስር እንዲላላ እየተደረገ÷ አገራችንን ከጊዜ ወደጊዜ እየከፋ በሚሄድ ሁለንተናዊ ቀውስ ውስጥ እያስገባት ይገኛል፡፡

ሕዝባችን የተዋደቀው÷ መስዋዕትነት የከፈለውና አሁንም ፍዳውን እየቆጠረ የሚገኘው ዘለቄታዊ መረጋጋትን አግኝቶ መብቶቹን ለሚያስከብርበት በእርቅና ሰላም ላይ ለተመሠረተ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት ለመሆን ነው፡፡ ይኸንን የረጅም ጊዜ ተጋድሎ በግንቦት ሰባት ዘጠና ሰባት ምርጫ በእጁ ለማድረግ ችሎ ነበር፡፡ ሕዝባችን ድሉን ሊያስከብርበት የሚችል ድርጅታዊ ብቃትና ጥንካሬ ስላጠረው እነሆ የአቶ መለስ አምባ-ገነን አገዛዝ የሽብር ጦርነት አውጆበት ድሉን በጠብ-መንጃና በአመፅ ተቀምቶ ለግፍ ግድያ÷ እስራት÷ ረሃብ÷ እንግልት÷ መፈናቀልና ስደት ተዳርጎ ይገኛል፡፡ ድሌን ያስጠብቁልኛል÷ መብቴን ያስከብሩልኛል ብሎ የጠበቃቸው÷ እነሱም ቃል የገቡለት መሪዎቹም ቆራጦቹ "እምነት እስከ ሞት" ብለው በእምነታቸው ለእስር ሲዳረጉ ከፊሎቹ ለሽብርተኛው አምባ-ገነን ጌታ-አደርነት ገብተው ትግላቸውና ሰልፋቸው ለሕዝብና ከሕዝብ ሳይሆን የገዥው ክፍል ተለጣፊ÷ አጫፋሪና ለየግል የሥራ ዋስትና ተሰልፈው በማየቱ አዝኗል፡፡

እንደሚታወቀው አገራችን የምትገኘው የቀውስ ቋትና አደገኛ ተብለው ከሚጠሩ የዓለም ክፍሎች ውስጥ አንዱ በሆነው የአፍሪቃ ቀንድ ነው፡፡ ይኸ የሰው ልጅ ዝርያ መገኛ ክፍለ-ዓለም በአብዛኛው ሰው-ሰራሽ በሆነ ጦርነትና ችጋር÷ አዘውትሮ በተጠናወተው የዝናብ እጥረት ሳቢያ በሚከሰት ድርቅ ምክንያት ለአስከፊ ጠኔና ለዘግናኝ እልቂት እየተዳረገ የሰው ልጅ አፅም መታየት እንደልማድና እንደ አይቀሬ ክስተት እየተቆጠረ ያለበት÷ ለዕለት ጉርሱ እንኳን እራሱን መቻል አቅቶት በአሳፋሪ ሁኔታ የዓለም ተመጽዋች ሕዝብ የሚኖርበት ቀጠና ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡

ለሕዝባቸው ሳይሆን ለሥልጣናቸው ብቻ የቅድሚያ ቅድሚያ የሚሰጡ አምባ-ገነኖች ደግሞ ይኸንን ያላስፈላጊና ሊወገድ የሚችልም የሚገባም አሳፋሪና ዘግናኝ የሰው ልጅ ሰቆቃ


ዋና መሥሪያ ቤት (Main Office)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box 73246
Washington, D.C. 20056-3246,U.S.A
ስልክ/Tel.: 202-291-4217;
ፋክስ/Fax: 202-291-7645

ኢትዮጵያ (Ethiopia)
ፖ.ሣ.ቁ./P.O.Box
Addis Abeba,Ethiopia
ስልክ/(Tel.) 251_______
ፋክስ/Fax:2511________

አውሮጳ (Europe)
Jonathan Str. 82
2524 JJ The Hague,
Netherlands
Tel/Fax 31 70 394 6132

እንዲያከትም በማድረግ ፋንታ በአንድ መልኩም ይሁን በሌላ ለሥልጣናቸው ማቆያና ለአገዛዛቸው ዕድሜ መቀጠያ መጫዎቻ የገበጣ ጠጠር አድርገው ይዘውታል።

እንደሚታወቀው መብቱን የተቀማ ሕዝብ የዕድሉ ወሳኝ ሊሆን ከቶውንም አይችልም። በዚህ የአፍሪቃ ቀንድ የሚገኘው ሕዝብ በሰላም፥ በመደጋገፍና በመከባበር በመልካም ጉርብትና መርኅ ብቻ ሳይሆን በጠበቀ የወንድማማችና የእህትማማች መንፈስ መኖር የሚችልበትና ለጋራ እድገቱና ብልጽግናው የሚተባበርበት ሁኔታ እንዳይፈጠር ከቅኝ ገዥዎች ጀምሮ ብዙ በሩቅም ሆነ በቅርብ ያሉ የውጭ ኃይሎች የሐይማኖት፥ የጎሣ፥ የአካባቢ፥ ወዘተ.. መሰናክሎችን እንደተበተቡ ግልጽ ቢሆንም፥ ለሕዝብ መቀራረብና ሰላም አለመኖር፥ ለአሳፋሪ ድህነትና ከዘመናዊ ሥልጣኔ ወደኋላ መቅረት ዋና ተጠያቂና ከሁሉም መሰናክል አይሎ የሚገኘው በየአገሮቹ ያሉ መንግሥቶች ሕዝባቸውን እስረኛ አድርገው በመያዛቸው ምክንያት ሕዝቡ ከአምባ-ገነኖች ነፃ በአለመሆኑና የሥልጣኑ ባለቤት መሆን በአለመቻሉ ነው።

አገራችን ከድንበሯ ውጭ በተስፋፊነት ጎረቤቶቿን የወረረችበትም ይሁን በአጥቂነት የተሰለፈችበት ጊዜ የለም። ሠራዊቷን ከድንበሯ ውጭ ያሰልፈችበት ጊዜም ቢሆን በቀረበ የድረሱልኝ ጥሪ እርዳታ ለመስጠት ብቻ እንደነበር ግልጽ ነው። በዘመነ አክሱም አሁን የመን ተብሎ በሚጠራው የቀይ ባሕር ማዶ ክፍል በአዝማች አብርሃ መሪነት የተደረገውም ይሁን በዘመናችን በኮርያና በኮንጎ የተከፈለው መስዋዕትነት ለሌሎች መብትና ሰላም መከበር የተደረጉ እንጅ የወራሪነት ተግባሮች አልነበሩም። አገራችን በተደጋጋሚ ጥቃት ሲደርስባት፥ ድርቡሾች ጎንደር ድረስ ዘልቀው ሲያቃጥሉም ሆነ የሰይድ ባሬው እብሪተኛ ተስፋፊ በየጊዜው ሲተናኮልና ሐረር ድረስ ዘልቆ ንጹኃንን ሲጨፈጭፍ፥ አጥቂውን ወደመጣበት ከመመለስ ውጭ አቅም በነበረበት ጊዜም ሆነ ማድረጉ ከአግባብ ውጭ በማይሆንበት ሁኔታም እንኳ ቢሆን ኢትዮጵያ ድንበር ተሻግራ በሌላ አገር ላይ ሠራዊቷን አስፍራ ወይም ወረራ አድርጋ አታውቅም።

በማንኛውም ወታደራዊ ፍልሚያ አስቀድሞ ጥቃት መሰንዘር የሚያስፈልግበትና አግባብ የሚሆንበት ጊዜ እንደሚኖር የታወቀ ነው። ይኸ የሚሆነው ግን ግልጽ ጦርነት እየተካሄደ ባለበት ሁኔታ ብቻ ነው። በአሁኑ ጊዜ ለአገራዊ አንድነትም ሆነ ለብሔራዊ ጥቅም ደንታ ኖሮት በማያውቀው የአቶ መለስ አገዛዝ ወደ ሶማሌ ጦር በመላክ በሶማሊያ የውስጥ ጉዳይ የሚያደርገው ጣልቃ ገብነት በታሪካችን ካሁን በፊት ያልታየ አዲስ ክስተት ነው። ይኸ ድርጊት አገራችን በአሁኑ ጊዜ ያለችበትን ውጥንቅጥ ሁኔታም ሆነ በአሁኑ ጊዜ ያለውን የአካባቢ፥ የመካከለኛው ምሥራቅም ሆነ የዓለምን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ እጅግ አደገኛና ኃላፊነት የጎደለው፥ አገራችንን ወደተወሳሰበና ወደማያባራ ቀውስ ውስጥ የሚያስገባ እርምጃ ሆኖ አግኝተነዋል።
ማንኛም አገር ሉዓላዊነቱን ለማስጠበቅና ዳር ድንበሩን ለማስከበር አደጋን አስቀድሞ የመከላከል እርምጃ የመውሰድ መብት ሊኖረው ይችላል። ይኸ ደግሞ እንዲሁ እንዳሻውና በዘፈቀደ በሌጣው የሚተረጎም ጉዳይ አይደለም። ዳር ድንበርን ማስከበር የማንም መንግሥት ኃላፊነት መሆኑ ያለና የሚጠበቅ ሲሆን፥ አንድ መንግሥት ከሁሉም በላይ ያለበት ኃላፊነትና ግዴታ ግን የዜጎቹን ደኅንነት መጠበቅ ነው። ይኸ ደኅንነት ደግሞ ሰብኣዊ መብትንና አካላዊ ደኅንነትን ያካተተ ነው። አገራዊ ደኅንነት ደግሞ የሚያልፈው በሕዝብ (በዜጎች) ደኅንነት አድርጎ ነው። የአገር አንድነትና ሉዓላዊነት የማስከበርና የማስጠበቅ ተግባርም የመንግሥት ብቻ ሳይሆን የመላው ሕዝብ ኃላፊነትና ግዴታ ነው። ስለሆነም ሕዝባችን በከበረ መስዋዕትነቱ ያስጠበቀውና በደሙና በአጥንቱ የተለሰነው አገራዊ አንድነት እንዳይደፈርስ ነቅቶ የመጠበቅ ኃላፊነት የሕወሓት/ኢሕአዴግ ብቻ ሳይሆን ከሁሉምና ከማንም በላይ የመላ ሕዝባችን ነው። እንኳን ድንበር ተሻግሮ ለሚደረግ ግዳጅ ወይም ለሚወሰድ ዓቢይ እርምጃ ማንኛውም ለአገር አንድነትና ለብሔራዊ ክብር ወይም ለአካባቢ ሰላም የሚደረግ ወታደራዊ ዘመቻ አዎንታዊ ውጤት የሚኖረው ሕዝብን በቀጥታ ሲያሳትፍ፥ የሕዝብን ይሁንታ ሲያገኝና የሕዝብ ድጋፍ ሲኖረው ብቻ መሆኑ ሊታወቅ ይገባል። ማንኛውም ጦርነት አድራጊ ክፍል ጦርነት ውስጥ ከመግባቱ በፊት አስቀድሞ

*ማወቅ ያለበት የሚደረገው ጦርነት የሚያስከፍለውን መስዋዕትነት፥ የሚያስወጣውን ወጭና የሚያስከትለውን መዘዝ ነው፡፡ ወታደራዊ ጠበብት "የመጀመሪያዋን የጦርነት እርምጃ ከመውሰድህ በፊት የመጨረሻዋን እርምጃ እወቅ" እንዲሉ ነውና!*

*አገራችን ኢትዮጵያ በምሥራቁ ክፍለ ግዛቷ በኩል ከስድሳዎቹ ዓመታት ጀምሮ ያላባራና ቦግ እልም ሲል በቆየ በአብዛኛው በሶማሌ እብሪተኛ ተስፋፊዎች ቆስቋሽነትና አበረታችነት  በሚደረግ ፀረ-ኢትዮጵያና ፀረ-አንድነት ቡድኖች ስትደማ መኖሯ የታወቀ ነው፡፡ ስለሆነም ማንኛውም ኃላፊነት የሚሰማው ክፍል በሶማሌ ውስጥ የሚደረገው ሁሉ ቢያሳስበውና ልዩ ትኩረት ቢሰጠው የሚገባ ብቻ ሳይሆን የሚጠበቅ ነገር ነው፡፡*
*የአሁኑ የኢትዮጵያ ገዥዎች ወደሥልጣን ሲመጡ የቀድሞ የሰይድ ባሬ መንግሥት ያደረገላቸውን ውለታ ለመመለስ በሚመስል መልኩ የሶማሌ የጦር መኮንኖችና ባለሥልጣኖች ተደራጅተው በኢትዮጵያ ምሥራቃዊ ክፍል ባቋቋሙት የጎሣ ክልል ኃላፊ እንዲሆኑ ማድረጋቸው ለአገሩ አንድነት የተዋደቀውን የአካባቢው ኗሪ ግራ ያጋባና ከልብ ያሳዘነ፥ የቀረውን ኢትዮጵያዊ ሁሉ ያስቆጨ ተግባር እንደነበር የሚታወስ ነው፡፡*
*አሁን በኦጋዴን ብሔራዊ ነፃ-አውጭ ግንባር ስም ኦጋዴንን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል ዓላማው አድርጎ የሚንቀሳቀሰው ቡድንም ሆነ በሶማሊያ የስላሞች ፍርድ ሸንጎ ተብሎ የሚጠራውና በአክራሪነት የሚጠረጠረው ኃይል የሚመሩት ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ አቋም ባላቸው የቀድሞ የሰኢድ ባሬ የጦር አበጋዞች ነው፡፡*
*ላለፉት አሥራ-አምስት ዓመታት ማዕከላዊ መንግሥት አልባ ሆና የቆየችውን ሶማሌን አንድ ለማድረግ በማሰብ ቀደም ሲል በአፍሪቃ አንድነትና በተባበሩት መንግሥታት የሚደገፍ ልዩ ልዩ የጦር ተፋላሚ አውራዎችን ያቀፈ "የሽግግር መንግሥት" በኬንያ መቋቋሙ ይታወቃል፡፡ በስንት መጓተት ከኬንያ ወደ ሱማሌ የተዛወረው ይኸ የሽግግር "መንግሥት" በስም ካልሆነ በስተቀር በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያለው አስተዳደር ዘርግቶ አገሪቱን መቆጣጣረና ማረጋጋት ቀርቶ ኅልውናውን ማቆየት ተስኖት በባይደዋ መንደር ተወስኖ በወያኔ/ኢሕአዴግ ዘበኛነት በጣረ ሞት ላይ ከሆነ ውሎ አድሯል፡፡ አምሳያ ፍለጋ ይመስል ይኸንን በራሱ ሕዝብ ዘንድ ተቀባይነት ያጣ ቡድን በሕይዎት ለማቆየት የአቶ መለስ አገዛዝ በወሰደው እርምጃ ምክንያት ኢትዮጵያን "ታሪካዊና የምር" ጠላት አድርጎ የሚቆጥረው የእስላሞች ፍርድ ሸንጎ የአገሪቱን ዜጎች አገርን ከወራሪዎች ለማዳን በሚል ጥሪ ሁኔታው አዲስ ዓይነት አሰላለፍ እንዲኖረው ከፍተኛ አስተዋጽዖ እያደረገ ነው፡፡ ጥሪውም "አገርን ከወራሪ መከላከል" በሚል ብቻ የተወሰነ ሳይሆን "ከሐይማነት-የለሽ የኢትዮጵያ ወራሪዎች" የሚል ሐይማኖት ጋር እንዲያያዝ ተደርጎ እየቀረበ ነው፡፡ በአለው ሁኔታ የኢትዮጵያ ሠራዊት በሶማሌ ምድር እንዲኖር ማድረግ ነገሩን የሚያባብስ ከመሆኑ ሌላ የጠቀመው በአክራሪነት የሚከሰሰውን ቡድን ብቻ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በመሆኑም የኢትዮጵያ (የኢሕአዴግ) ጣልቃ መግባት በአንድ በኩል ለደካማው "የሽግግር መንግሥት" የበለጠ መዳከምና በአክራሪነት ለሚከሰሰው ክፍል የሶማሌን ሕዝብ በብሔራዊ ስሜት በመቀስቀስ ሊያገኝ ከሚችለው በላይ ደጋፊ እንዲያሰባስብና እንዲጎለብት በማድረግ፥ በሌላ በኩል የሌሎችን ጣልቃ-ገብነት በማፋጠኑ በኩል ከፍተኛ አስተዋጽዖ እንዳደረገ ግልጽ ሲሆን በአኳያው አገራችንን ለባሰ ጥቃት የሚያጋልጥ ሁኔታን ፈጥሯል፡፡*
*በዚህ ውጥንቅጥ አሰላለፍ የአካባቢም የዓለም-አቀፍም ኃይሎች ከሸዓቢያዋ ኤርትራ እስከ ኢራን በአንድ በኩል፥ ከኬንያ እስከ አሜሪካ በሌላው በኩል ተደርድረውበት ይገኛል፡፡ ይኸ መቋጫ የሌለውና አጠቃላይ ትርምስን የሚጋብዝ አሰላለፍ ሲታይ የሶማሌ ጉዳይ ከሶማሌ የውስጥ ጉዳይነት አልፎ ከአካባቢ ችግርና ውዝግብነት የዘለለና ዓለም-አቀፍ ይዞታ ያለው አደገኛ ሁኔታ እየሆነ መጥቷል፡፡*

*ቀደም ሲል እንደጠቀስነው ኢትዮጵያ እንደ አገር ዳር ድንበሯን ለማስከበርና ከውጭ ሰላም አደፍራሾች እራሷን የመከላከል ሕጋዊ መብት አላት፡፡ እያደገ የሚመጣንና አይቀሬ አደጋንም አስቀድሞ ማጨንገፍ የተለመደ ወታደራዊ ስልት ነው፡፡ ሆኖም አሁን በሕወሓት/ ኢሕአዴግ እየተወሰደ ያለው እርምጃ ጊዜውንና ሁኔታውን የጠበቀ አይደለም፡፡*

የሶማሌ ሕዝብ የመረጠውን የመንግሥት ዓይነት የማቋቋም መብቱን ማንም ሊወስንለት አይችልም፣ አይገባምም። ሆኖም በሶማሌ ውስጥ በአፍጋኒስታን እንደነበረው ዓይነት የታሊባን አክራሪ ኃይል ሥልጣን ቢይዝ ለሶማሌ ሕዝብም ይሁን ለአካባቢው አገሮችና ሕዝብ ላይጠቅም ይችላል ብሎ ማሰብና ሊያስከትል የሚችለውን አገናዝቦ አስፈላጊውን ክትትልና ጥንቃቄ ማድረግ ደግሞ የማንኛውም ኃላፊነት የሚሰማው ክፍል መብትም ግዴታም መሆኑ ከቶውንም ሊዘንጋ አይገባም። በዚህ ረገድ የሶማሌ ጎረቤት ብቻ ሳይሆን የጎሣ ትስስርና ዝምድና የሚጋሩት ኢትዮጵያ፥ ኬንያና ጅቡቲ የጠነከረ ተሃስቦአቸውን ቢገልጹ አግባብነት አለው። ከሁሉም በላይ ደግሞ ኢትዮጵያ የተለየ ትኩረት ለጉዳዩ ብትሰጥ የሚፈረድ አለመሆኑ ብቻ ሳይሆን አዲስ የሚሆነው ለሁኔታው ተገቢ ትኩረት ባትሰጥና አስፈላጊ ዝግጅት ባታደርግ ነው። ምክንያቱም ኢትዮጵያ በዚህ ቀጠና ስትደማ የኖረች ብቻ ሳይሆን አዲሶቹ በአክራሪነት የሚጠረጠሩት መሪዎችም ይሁኑ በኦጋዴን ነፃ-አውጭ ስም የሚንቀሳቀሰው ተገንጣይ ቡድን የኢትዮጵያን አንድ አራተኛ የሚሆን ክፍል ቆርሶ ወደ ሶማሌ ለመቀላቀል ያላቸውን ሃሳብ ብቻ ሳይሆን ቁርጠኝነት በአደባባይ አውጀዋልና ነው። በተጨማሪም ይኽንን ስጋትና ተሃስቦ ጠንከር የሚያደርገው ከሸዓቢያ ጀምሮ ያሉ ፀረ-ኢትዮጵያ ኃይሎች ለዚህ እውንነት ያልተቆጠበ እርዳታቸውን እንደሚሰጡ በገሃድ እየታየ ነው። ሁሉም በግልጽ ሊረዳው የሚያስፈልገው ጉዳይ አሁን ያለው ሁኔታ እንዲሁ በግልቡ እንደሚታየው ቀላል አለመሆኑን ነው። የተፈጠረው ሁኔታ እጅግ ውስብስብና ለአካባቢው በተለይ ደግሞ ለኢትዮጵያ አጥብቆ የሚያሳስብም የሚያሰጋም እንደሆነ ይገነዘቧል።

ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት ሐይማኖቶች ታላላቆቹን እምነቶች፥ እምነተ-ኦሪትን፥ ክርስትናንና እስልምናን ቀድማ ያስተናገደች አገር መሆኗ የታወቀ ነው። ኢትዮጵያችን ሁለቱ ታላላቅ ሐይማኖቶች ተቻችለው ያደጉባት አገር መሆኗ በአድናቆትና በኩራት የምንዘክረው ነው። ምንም እንኳ አሁን ያለው የኃይል አሰላለፍ ቀደም ሲል ከሚታወቀው ፀረ-ኢትዮጵያ የኃይል አሰላለፍ በቅርጽ ብዙም የተለየ ባይሆንም በዚህ ረገድ ሁኔታውን ይበልጥ አሳሳቢ የሚያደርገውና ሁሉም ጠንቅቆ ሊገነዘብ የሚገባው ጉዳይ ግን አሁን ያለው የኃይል አሰላለፍ አዲሱን ዓይነት "የአክራሪ ሐይማኖተኛ" ልባስ እየያዘ መምጣቱ ይዘቱን በጣም የተለየ የሚያደርገው መሆኑን ነው።

ምን ጊዜም ቢሆን አምባ-ገነኖች ሁሉንም ሁኔታ የሚያዩበት መነጽር የሚፈልጉትንና የሚያልሙትን ብቻ ስለሆነ የአቶ መለስ ሕወሓት/ኢሕአዴግ በውስጥም በውጭም ተቀስፎ ከተያዘበት ዙሪያ ጥምጥም ችግር እፎይታን ለማግኘትና አቅጣጫ ለማስቀየር ከጥቂት ዓመታት በፊት በባድሜ እንደታየው የኢትዮጵያን ሕዝብ ቀልብ በሳበ መልኩ አነሳስቶ ከጎኑ በማሰለፍ ሸክሙ እየከበደበት የመጣውን ጫና ለማቅለል አስልቶ ይኽንን የሶማሌ ሁኔታ ለመጠቀም አያስብም ማለት አይቻልም። እንዳልሆነ ማረጋገጫ ስለማይኖር፥ አገዛዙ አሁን በሱማሌ እየወሰደ ያለው እርምጃ ከዚህ ስሊት ተነስቶ ከሆነ በውነቱ እጅጉን የተሳሳተ ስሊት ብቻ ሳይሆን ዕብደት ነው። ይኽ ሲባል ግን የጉዳዩ ክብደት ሳይመዘን ማንኛውም በሕወሓት/ኢሕአዴግ የሚወሰድ እርምጃ እሱ ስለወደደው ብቻ ልንቃወም ይገባል ማለት አይደለም። ማንም ኃላፊነት የሚሰማው ክፍል በምንም መንገድ ኢትዮጵያን የሚያያት አገዛዙን በሚያይበት ዓይን ሊሆን አይችልም። ስለሆነም አንዳንድ አገዛዙ የሚወስዳቸው ሕጋዊና ተገቢነት ያላቸው፥ በሕዝብም በተቃዋሚውም ጭምር ሊደገፉ የሚገባቸው እንደተፈጥሮ አደጋና የውጭ ወረራ የመሳሰሉትን ለመከላከል የሚደረጉ እርምጃዎች እንደሚኖሩ መታወቅ አለበት። በእንደዚህ ዓይነት አገራዊ ሁኔታ ሥልጣን ላይ ያለው ኃይል ማንም ይሁን ማን ማንኛውም ዜጋ እንደ አንድ አገር ሕዝብ በጋራ የመቆም ኃላፊነት እንደሚኖርበት ኅብረቱ ያምናል። ሆኖም ኅብረቱም ሆነ ማንኛውም በአገር አንድነትና በሕዝብ ደኅንነት ጉዳይ ላይ ኃላፊነት የሚሰማው ወገን ሁሉ የሕወሓት/ኢሕአዴግ መሪዎች የሚወስዱትን እርምጃ በጥርጣሬ ዓይን ቢመለከትና አመኔታ ባይኖረው ሊገርም አይገባም። አሁንም ሆነ ወደፊት በዚህ አምባ-ገነን አመራር የሚወሰድ እርምጃ <u>የኢትዮጵያን ብሔራዊ ጥቅም በሚያስጠብቅ መልኩ እንደማይቋጭ (እንደማይደመደም)</u> መጠራጠር ተገቢ መሆኑ

የብዙ አሥርተ ሽህ ዜጎቻችንን ሕይዎት ደመ-ከልብ ያደረገውን በባድመ ምክንያት ከሽዓቢያ ጋር የተደረገውን ከንቱ ጦርነት ማስታወሱ በቂ ትምሕርት ሊሰጠን ስለሚገባ ነው፡፡

በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ ሕዝብ የመረጣቸው መሪዎቹና በርካታ ንፁህ ኢትዮጵያውያን ያለአግባብ ታስረው፥ የዜጎች መሠረታዊ መብቶች ተነፍገውና ተረግጠው ባሉበት፥ ሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥታዊ ባህሪውን አጥቶ ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብቻ ሳይሆን ከራሱም ተጣልቶና ተነጥሎ፥ ከሕዝብ ጋር ሆድና ጀርባ ሆኖ እርቃኑን ባለበት፥ አገራችን አገራዊ አንድነቷና የውስጥ ሰላሟ አስተማማኝ ባልሆነበትና የተደራረቡ ችግሮች ባሉበት፥ የሶማሌ የውስጥ ጉዳይ መደበኛ የውስጥ ጉዳይ ከመሆን አልፎ ዓለም-አቀፋዊ ይዞታ ላይ ባለበት፥ ከሁሉም በላይ አደገኛ በሆነና ከአሁን በፊት ምናልባትም ከአሥራ-ስድስተኛው ክፍለ-ዘመን ወዲህ ታይቶ ባልታወቀ መልኩ ለየት ያለ ሐይማኖታዊ ባህሪ በያዘበትና መዘዙ እንደሰደድ እሣት መቆጣጠር ወደማይቻልበት ደረጃ ሊቀጣጠልና አጠቃላይ ትርምስ ሊጋብዝ በሚችልበት ሁኔታ፥ በአቶ መለስ አምባ-ገነን አገዛዝ የተወሰደው በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ የመግባት መስመሩን የሳተ እርምጃ በከፍተኛ ደረጃ ኃላፊነት የጎደለውና ፍጹም ደንታ ቢስ ድርጊት ሆኖ አግኝተነዋል፡፡
ስለሆነም፤

1ኛ) የሕወሓት/ኢሕአዴግ መንግሥት በሶማሌ ግዛት ውስጥ ያሰማራቸውን የመከላከያም ይሁን የፀጥታ ክፍል አባላት በአስቸኳይ አስወጥቶ በኢትዮጵያ ድንበር ውስጥ እንዲመልስና ከውጭ የሚሰነዘርን ማንኛውንም ጥቃት በአገሩ ምድር ላይ ሆኖ እንዲከላከል እንጠይቃለን፤

2ኛ) የኢትዮጵያ ሕዝብ አገዛዙ በወሰደው አርቆ ማየት የተሳነውና ሁኔታን ያላገናዘበ እርምጃ ምክንያት ከማንኛውም ኃይል የሚቀርብ ሐይማኖትንም ሆነ ጎሣን መሠረት ያደረገ ቅራኔና የርስ በርስ ግጭትን የሚፈጥር ጥሪ እንዳይቀበልና በተለመደው ጨዋነቱና አስተዋይነቱ ከእንደዚህ ዓይነት ከፋፋይና አደገኛ አዝማሚያት እንዲርቅ ወገናዊ ጥሪያችንን በአክብሮት እናቀርባለን፤

3ኛ) በሶማሌ ውስጥም ሆነ ከሶማሌ ውጭ በዓለም ዙሪያ የሚገኘው የሶማሌ ሕዝብ በሰኢድ ባሬ ተደጋጋሚ ወረራ ምክንያት የኢትዮጵያ ሕዝብ ወንድሙን የሶማሌን ሕዝብ ተጠያቂ አድርጎ እንደማያውቅ ሁሉ፥ አሁን የሶማሌን የሽግግር መንግሥት በመደገፍ ስምና በነሱም በተደረገ የእርዳታ አድርጉልኝ ጥሪ ሳቢያ በኢሕአዴግ የተወሰደውን እርምጃ የኢትዮጵያ ሕዝብ ያልመከረበት፥ ያልደገፈውና የማያገባው ጉዳይ ብቻ ሳይሆን በሶማሌ የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ መግባት አድርጎ እንደሚቆጥረው እንዲገነዘብና ለዘመናት ተቻችሎ የኖረው በሶማሌና በኢትዮጵያ ወንድማማች ሕዝብ መኻል የባሰ ደም መፋሰስና ትርምስ እንዳይፈጠር በተለይ ሐይማኖትን መሠረት በሚያደርግ ፀረ-ኢትዮጵያ እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዳይሆን ጥሪያችንን እናስተላልፋለን፤

4ኛ) በመሠረቱ ለሶማሌ የውስጥ ችግር መፍትሄ ሰጭው በቅድሚያ ባለጉዳዩ የሶማሌ ሕዝብ ነው፡፡ ይሁንናም አሁን ባለው የውስጥ ትርምስና የገቡ የውጭ እጆች ብዛት ሲታይ የሶማሌ ሕዝብ ይኸንን የውስጥ ጉዳዩን የመፍታት ዕድል የሚሰጥ አመች ሁኔታ ሊፈጠርለት ስለሚገባ፥ ዓለም-አቀፉ ኅብረተሰብ ቀደም ሲልም የሽግግር መንግሥቱን በማቋቋም ረገድ የረዳና በሁኔታውም ገና ከጅምሩ አንስቶ በጉዳዩ ያለበት ስለሆነ፥ ይኸንን ያንዣበበ አይቀሬ ትርምስና የሰው እልቂት ማስወገድ ግዴታ ስላለበት፥ የተባበሩት መንግሥታት የፀጥታው ምክር ቤት አስቸኳይ ስብሰባ ተጠርቶ አንድ የሶማሌ ማረጋጊያና ደኅንነት ውሳኔ እንዲያስተላልፍ እያሳሰብን፤ በዚህ ውሳኔ መሠረትም ገለልተኛና በአብዛኛው የእስልምና ሐይማኖት ተከታይ ከሆኑ አገሮች የተውጣጣ ዓለም-አቀፍ የሶማሌ አረጋጊ ኃይል ተቋቁሞ ሶማሌ ውስጥ በፍጥነት ተሠማርቶ ፀጥታውን እንዲያስከብርና ለሰላማዊ ሕዝብ ሰብዓዊ እርዳታ እንዲደርሰው እንዲደረግ እንጠይቃለን፤

(በዚህ የዓለም-አቀፍ የፀጥታ አስከባሪና አረጋጊ ኃይል ውስጥ የሶማሌ ጎረቤት አገሮች በምንም መንገድ ተሳታፊ መሆን እንደማይኖርባቸው ማሳሰብ እንወዳለን::)

5ኛ) ለሁለቱም ወገኖች በልዩ ልዩ ምክንያት ቀጥተኛ እርዳታ ለመስጠት የገቡ የውጭ ኃይሎች ሁሉ በአስቸኳይ የሶማሌን ምድር ለቀው ወደየመጡበት እንዲመለሱ እንጠይቃለን፤

6ኛ) ሁለቱም ተፋላሚ የሶማሌ ኃይሎች ማለትም ደካማው የሽግግር መንግሥትና የእስላሞች ፍርድ ሸንጎ አስቸኳይ የተኩስ ማቆም ስምምነት እንዲያደርጉ፣ ታጣቂዎቻቸውን በስምምነት በተወሰኑ ቦታዎች እንዲከቱና የሰላሙን መንገድ እንዲመርጡ እናሳስባለን፤

7ኛ) ቀደም ሲል በሁለቱ ተፋላሚዎች መኻል የተጀመረው ድርድር በአስቸኳይ በተባበሩት መንግሥታት፣ በአፍሪቃ አንድነትና በአረብ ሊግ አማካይነት እንዲቀጥል እናሳስባለን፤

8ኛ) በውጭ የሚገኘው ኅብረተሰባችን በዚህ መዘዙ እጅግ አደገኛ በሚሆን የአገርና የአካባቢ ሁኔታ ላይ የሰከነ ውይይትና ምክክር በማድረግ ከስሜታዊነት በፀዳ መልኩ በጠራ ግንዛቤ ላይ የተመሠረተ ኃላፊነት የተሞላበት አቋም መያዝ እንዲቻል፣ የፖለቲካ ድርጅቶች ከሲቪክና የሙያ ማኅበራት ጋር በማበር ከያዝነው የሳምንት መጨረሻ ጀምሮ በየከተሞች የጋራ ስብሰባዎች በጋራ እንዲጠሩና ኢትዮጵያውያን ተሳታፊ እንዲሆኑ እነሆ ለሚመለከታቸው ሁሉ ወገናዊ ጥሪያችንን እናቀርባለን፤

9ኛ) ከአሁን በፊት በተደጋጋሚ እንዳቀረብነው ሁሉ ከአንድ ጥፋት ወደ ባሰ ጥፋት እየዘለለና ውድ አገራችንን ለነሱም ሆነ ለማንኛችንም እንዳትሆን ወደሚያደርግ አደገኛ ሁኔታ እየወሰዳት ያለውን ገዥውን ፓርቲ ሕወሓት/ኢሕአዴግን ትርጉም ወዳለው ድርድር አስገድዶ ለማምጣት እንዲቻል በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉ የፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክና የሙያ ማኅበራት በአገራዊ አንድነት፣ በሕዝብ ሉዓላዊነት፣ በሕግ የበላይነት፣ በእኩልነትና በዴሞክራሲ ሥርዓት መርኅዎች ላይ የተመሠረተ ጠንካራ የጋራ መድረግ እንዲፈጠር ሁሉን-አቀፍ ስብሰባ በአስቸኳይ እንዲደረግ ጥሪያችንን እናቀርባለን፤

10ኛ) በተለይ አሁን የተፈጠረው ሁኔታ የጋራ አገራችንንና ሕዝባችንን ወደ ከፍተኛ አዘቅትና አጠቃላይ ትርምስ ውስጥ የማስገባቱ አደጋ እያየለ መምጣቱ ግንዛቤ ተወስዶበት፣ “ሳይቃጠል በቅጠል” እንዲሉ ሁኔታው ከቁጥጥር ውጭ ከመሄዱ በፊት ብሔራዊ መግባባትን ስለሚጠይቅ፣ የገዥው ፓርቲ ኃላፊዎችና አባላት በኖ የሚጠፋው ሥልጣንና ጊዜአዊ ጥቅም ሳይሆን የሩቁና ዘለቄታዊው የአገራችንና የሕዝባችን ጥቅም ታይቶአቸው የታሰሩ መሪዎችና የፖለቲካና የኅሊና እስረኞችን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በአስቸኳይ እንዲፈቱና ተቃዋሚው ክፍል በተደጋጋሚ ላቀረብነው ለሁሉን-አቀፍ አገራዊ እርቅና ሰላም ጉባዔ ሁኔታዎችን እንዲያመቻቹ ጥሪያችንን እናቀርባለን፤

በግባታዊነትና በጀብደኝነት እርምጃ አገር የባሰ አደጋ ላይ እንዳትወድቅ መከላከል የሁሉም ኃላፊነት ነው:: የኢትዮጵያ ሕዝብ በአንድነቱ ላይ የሚሰነዘርን ማንኛውም ጥቃት በተለመደው አኩሪ ኅብረቱ እንደሚቋቋምና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ማንኛውንም የውጭ አደጋ ከምንጩ ለማድረቅ ሕዝባችን በአንድነት እንደሚሰለፍ እምነታችን የጠና ነው:: በዚህ ረገድ ከሶማሌም ሆነ ከማንኛውም ክፍል በአገሪቱ ላይ የሚሰነዘርን ጥቃት ለመከላከል አስፈላጊው ዝግጅት ሁሉ መደረጉና በንቃት መጠበቁ ተገቢ መሆኑን ማሳሰብ እንወዳለን::

ያላስፈላጊ ጣልቃ-ገብነት በአስቸኳይ ይቁም!
እርቅና ሰላም ይቅደም!!
አንድነታችን በነፃነታችን፤ ነፃነታችንም በአንድነታችን!!

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት / ኅዳር ፲፰ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ/ም